JW.ORG
ይህን ፒዲኤፍ ከwww.jw.org/am ላይ ማውረድ ትችላለህ

# የያዕቆብ ወንዶች ልጆች

## ዘፍጥረት ምዕራፍ 37

**የልጆቻችሁን ስሜትና ፍላጎት ግምት ውስጥ በማስገባት ተስማሚ የሆኑ መልመጃዎችን ምረጡ። ከዚያም መልመጃዎቹን በቤተሰብ ሆናችሁ ሥሩ።**




## ዘፍጥረት ምዕራፍ 37ን አንብቡ

ቀጥሎም ሥዕላዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን አንብቡ (ኢንተርኔት ላይ እንዳላችሁ ወይም በወረቀት አትማችሁ ማንበብ ትችላላችሁ)፤ ከዚያም መጨረሻ ላይ የሚገኙትን ጥያቄዎች ተወያዩባቸው።

**እንዲህ አድርጉ፦** ልጆቻችሁ ያዕቆብ ለዮሴፍ ያሠራለትን ልብስ እንዲስሉ ንገሯቸው። ልብሱ ምን እንደሚመስል ለማወቅ *የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች መማሪያ መጽሐፌ* የተባለውን መጽሐፍ ምዕራፍ 19 ተመልከቱ። እንዲሁም ልብሱ ምን እንደሚያመለክት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት www.jw.org የተባለው ድረ ገጽ ላይ PUBLICATIONS > ONLINE LIBRARY በሚለው ሥር *Insight* የተባለውን መጽሐፍ አውጡ፤ ከዚያም “Dress” እና “Joseph” የሚሉትን ርዕሶች ተመልከቱ።*

* በዚህ ታሪክ ላይ ተመሥርቶ የተሠራ ድራማ በአንዳንድ ቋንቋዎች ማግኘት ትችላላችሁ። “ፐሪዘርቪንግ ላይፍ ኢን ታይም ኦቭ ፋሚን” በተባለው በዚህ በድምፅ የተቀዳ ድራማ ላይ ከዚህ ቀጥሎ በሚወጡ ሥዕላዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ላይ የተጠቀሱ ታሪኮች ይገኛሉ። ይህን ድራማ www.jw.org ከተባለው ድረ ገጽ ላይ ማውረድ ትችላላችሁ።

## ልታትሟቸው የምትችሉ ሌሎች መልመጃዎች



### የሥዕል ጨዋታ

**በዚህ ሥዕል ላይ ምን ስህተቶች ይታዩሃል?** (ለትናንሽ ልጆች የተዘጋጀ)፦ ልጆቻችሁ፣ በሥዕሉ ላይ የሚታዩትን ሁለት ስህተቶች እንዲፈልጉ አድርጉ። ከዚያም መልሳቸውን በክፍት ቦታው ላይ እንዲጽፉና ሥዕሉን ቀለም እንዲቀቡ ንገሯቸው። ሥዕሉ ምን እንደሚገልጽ ጠይቋቸው።



### ለጥናት የሚረዳ መልመጃ

**እኔ ማን ነኝ?** (ትንሽ ከፍ ላሉ ልጆች የተዘጋጀ)፦ ልጆቻችሁ፣ የተሰጡትን ፍንጮች ካነበቡ በኋላ በክፍት ቦታዎቹ ላይ የያዕቆብን ልጆች ስም እንዲጽፉ አድርጉ።



### ካርድ በመሰብሰብ መማር

**የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ካርድ፤** በአጭሩ የቀረበውን ታሪክ አንብቡ። በካርዱ ላይ የሚገኙትን ጥያቄዎች ልጆቻችሁን ጠይቋቸው። ልጆቻችሁ በዚህ ካርድና በሌሎች ካርዶች ላይ የሚገኙትን የጊዜ ሠንጠረዦች በመመልከት ካርዶቹን በሚከተሉት ሁለት መንገዶች እንዲከፋፍሏቸው አድርጉ፦ (1) ኢየሱስ ከመወለዱ *በፊት* የኖሩ እና (2) ከኢየሱስ *በኋላ* የኖሩ።

www.jw.org/am © 2013 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania